Asylum Support Partnership
help and advice

September 2012 Amharic

# የጥገኝነት ድጋፍን ስለማመልከት

ጥገኝነት የሚፈልጉ ሰዎች ከዋናው የመንግስት ተረጂዎች ጥቅማ ጥቅሞች ያልተካተቱ ናቸው እና አብዛኞቹ ጥገኝነት ጠያቂዎች ስራ መስራት አይፈቀድላቸውም። ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ግን እንዲሰሩ ሊፈቀድላቸው ስለሚችል፡ ስለዚህ ሁኔታዎች ምክር ለማግኘት መፈለግ ይገባል።

ጥገኝነት የመጠየቅ ሂደት ረዘም ሊል ስለሚችል፡ እራስዎን እንዴት ለማገዝ እንደሚችሉ ማሰብ ይኖርብዎታል። ስለዚህ ከየእንግሊዝ አገር የዶብ ማሕበር UK Border Agency ( UKBA) ጽህፈት ቤት የሚገኙትን ድጋፎች ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ UKBA የሚባለው ማህበር ምንም ዓይነት የገንዘብ ገቢ የሌላቸው ችግረኛ ጥገኝነት ጠያቂዎችን የሚረዳ የመንግስት አካል ነው። UKBA የመኖርያ አገልግሎትና እንዲሁም ለምግብና ለልብስ የሚሆን የገንዘብ እገዛ ሊሰጥዎት ይችላል። የመኖርያ ቤት ካልዎት ለምሳሌ፡ ከጓደኞች እና ከዘመዶች ጋር የሚኖሩ ከሆኑ ‘subsistence support’ ('የድጎማ ድጋፍ') በመባል የሚታወቀውን የገንዘብ እገዛ ብቻ እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ።

ስለሆነ፡ ራስዎን መርዳት የማይችሉ ከሆነ፡ በጥገኝነት ጥያቄዎ ሂደት ላይ የጥገኝነት እዛ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። የጥገኝነት ይግባኝዎ በመሄድ ላይ እያላ ይጠቁሙ። ካስፈለግዎም፣ ጥገኝነት በጠየቁበት ተመሳሳይ ጊዜ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። UKBA ም ጊዜያዊ ማረፊያ ያዘጋጅልዎታል።

**ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች፡** ለጥገኝነት በግልዎ ያመለከቱ መሆንዎን ከተረጋገጠ በ UKBA ወይም/እና በማሕበራዊ አገልግሎት ጽህፈት ቤት እድሜዎ ከ 18 ዓመት በታች ከሆነ፡ የሚፈልጉትን እገዛ ከአካባቢው የሚገኝ ባለስልጣን ሊያገኙ ይችላሉ። የጥገኝነት ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ከፈለጉም እገዛ እንዲሰጥዎት ወድያውኑ ለማመልከት ይችላሉ።

## ከ UKBA እገዛ ለማግኘት ብቁ የሚሆነው ማን ነው?

የመኖርያና የገንዘብ ዕርዳታ ወይም የገንዘብ እገዛ ብቻ የሚያስፈልግዎት ሊሆን ይችላል። እንግዲህ እነዚህ እገዛዎችን ብቻ ለማግኘት በሚያመለክቱበት ወቅት ለ UKBA የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለብዎት።

- ለጥገኝነት ያመለከቱት ጥያቄ የተመዘገበና ማመልከቻው ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑን
- ምንም ገቢ የሌልዎት መሆኑን (ማለት ትንሽ ገቢ ወይም ምንም ገንዘብና መኖርያ ቤት እንደሌልዎት)
- እንግሊዝ አገር ከገቡ ለጥገኝነት ያመለከቱት 'በተቻለ መጠን በፍጥነት' መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
- ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በላይ መሆኑንዎን ማረጋግጥ ይገባል።

## 'በተቻለ መጠን በፍጥነት' ማለት ምን ማለት ነው?

ይህ ፈተና ለገንዘብና የመኖርያ ቤት እገዛ የሚያመለክቱ እንዲሁም የገንዘብ እገዛ ብቻ ለሚያመለክቱ ሰዎች የሚመለከት ነው። የገንዘብ እገዛ ለማመልከት ብቻ በሚፈልጉበት ጊዜ (ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የመኖርያና የገንዘብ እገዛ ወይም የገንዘብ እገዛ እያገኙ እያሉ ሆነው የገንዘብ እገዛ ብቻ ለማግኘት ለመቀየር የሚፈልጉ ከሆነ) UKBA ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ያስገባል፡

- ለጥገኝነት ያመለከቱበት ጊዜ፡ አገር ውስጥ በገቡ በሶስት ቀናት ውስጥ እንደሆነ፡
- ስለ አመጣጥዎ የሰጡት ዝርዝር መረጃ አሳማኝ መሆኑን፤



Asylum Support Partnership is a partnership project hosted by the British Refugee Council
British Refugee Council, (commonly called the Refugee Council) is a company limited by guarantee registered in England and Wales, [No 2727514] and a registered charity, [No 1014576].
Registered office: PO Box 68614, London E15 9DQ United Kingdom, VAT reg no: 936 519 988

UKBA በተለምዶ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዳመለከቱ ለማረጋገጥ፡ በተለምዶ የጥገኝነት ለመጠየቅ በሚያመለክቱበት ወቅት የሰጡት መረጃን ይመለከታል። ምናልባት UKBA እገዛውን ለመስጠት ለመወሰን የሚራስቸግረው ወይም ለጥግኝነት ያመለከቱበት በጊዜው አይደለም ብሎ ካሰበ ባለስልጣናቱ ለቃለ መጠየቅ ወደ Croydon፡ GlAsgow ወይም Liverpool እንዲመጡ ሊጠርዎት ይሆናል። ወደ Croydon ለመምጣት የማይቹሉ መሆንዎን ለ UKBA አስቀድመው ካሳወቁ፡ ቃለ መጠየቁ በሚኖሩበት አካባቢ ወደሚገኘው የጽህፈት ቤታቸው እንዲደረግልዎት ሊያደርጉ ይችላሉ። **እገዛ የሚያስፈግዎትና 'በተቻለ መጠን በፍጥነት' እንዳመለከቱ *መሆንዎን ለማሳመን ይህን የቃለ መጠይቅ ቀጠሮው ላይ መገኘት ይገባል፡***

ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ላይ ካሉ UKBA እርስዎን እገዛዉ አይከለክልም፡

ከ 18 ዓመት በታች ልጆች ያልው የቤትሰብ አካል ከሆኑ፡
ልዩ የሆነ እንክብካቤ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፡ ለምሳሌ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ፡ ልዩ እንክብካቤ የሚያስፈግዎት ከሆነ፡ በማህበረሰብ እንክብካቤ ህግ መሰረት በአካባቢዎ ወደሚገኘው ባለስልጣን ጽህፈት ቤት ሄደው ግምገማ እንዲደረግሎት ሙብት አልዎት። ይህን ግምገማ ከ UKBA እንዲጠይቁ የምክር ሰጪ ድርጅቶች ወይም የቤተሰብዎ አባል ሊረድዎት ይችላሉ።
ይህ መንግስት እገዛ ካልሰጥዎት፡ በአውሮፓ የሰብዓዊ ሙብቶች ውል መሰረት (European Convention on Human Rights) ባልሆነ ሁኔታ እንደሚሰቃዩና የሚዋረዱ መሆንዎን ማሳመን ከቻሉ፣ ይህን እርስዎን የሚመለከት መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለጉ፡ ህጋዊ የሆነ ምክር መፈለግ ይገባል።

እንግሊዝ አገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ እየኖሩ እያሉ፡ አገርዎ ውስጥ ያለው ሁኔታ ተቀይሮ ጥገኝነት የጠየቁ ከሆኑ፡ UKBA ይህን ማመልከቻ ያደረጉበት ጊዜ በተቻለ መጠን በፍጥነት መሆኑን ያጣራል።

## ለ UKBA እገዛ እንዴት ማመልከት አለብኝ?

በዚህ የመረጃ ጽሁፍ መጨረሻ ላይ የተረዘረዘሩትን የስደተኞች ጉዳይ ድርጅቶች እንዴት ለ UKBA እገዛ ማመልከት እንደሚችሉ ሊያስረድዎት ይችላሉ። እንዲሁም ሌሎች እንደ የዜጎች የምክር አገልግሎት (Citizens advice service) እና የስደተኞች ቡድኖች በዚህ ሁኔታ ላይ ሊያግዝዎ ይችላሉ። በማሰናበቻ ማዕከል ከታሰሩና በዋስ ለመፈታት ላቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ካገኙ፡ ከስደተኞች ማህበሮች አንዱ ለዚህ የ UKBA እገዛ ማመልከቻ ለማስገባት ሊተባበርዎት ይችላሉ።

## የመኖርያና የገንዘብ ድጋፍ እፈልጋለሁ

የመኖርያና የገንዘብን ድጋፍ ለማግኘት፡ ለሁለቱም ፍላጎትዎን አንድ ላይ ማመልከት ይችላሉ። ነገር ግን የ UKBA ጽህፈት ቤት ብቁ መሆንዎን አረጋግጦ ውሳኔ እስኪሰጥዎት ድረስ የሚኖሩበት ቦታ ከሌልዎት፡ የጥገኝነት ጥያቄዎን እስኪወሰን ድረስ የUKBA ጽህፈት ቤት በማስተዋወቂያው ማዕከል እንዲገቡ ወይም በጊዜያዊ የመኖርያ ማህበር እንዲቆዩ UKBA ጊዜያዊ ማቆያ እንዲሰጥዎት ሊልክዎት ይችላሉ። ይህ ጊዜያዊ ማቆያ የሚባለው ቦታዎች ጥገኝነት ጠያቂዎች ለአጭር ጊዜ የመኖርያ፣ የምግብና የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙባቸው ቦታዎች ናቸው።

### UKBA *መኖሪያ ሊሰጠኝ ከተስማማስ*

የ UKBA ጽህፈት ቤት እርስዎ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ነዎት ብሎ ከወሰነ፡ በተለምዶ ከለንደንና ከኢንግላንድ ደቡባዊ ምስራቅ ውጪ ወደሚገኙት ወደ አዲሱ የመኖርያ ቦታዎ እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ያመቻችልዎታል። UKBA ይህን 'ዲስፐርሳል' ሂደት ይጠራዋል። የዲስፐርሳል ማረፊያ ቦታዎ ልክ መጀመያ እንደተሰጥዎት የማረፊያ ቦታዎች ናቸው። በ UKBA በሚላኩበት ጊዜ የሚሄዱበትን ቦታ ለመምረጥ አይችሉም፡ ሆኖም ግን የአካላዊና ግላዊ ሁኔታዎን ግምት ውስጥ ያስገባሉ። UKBA ወደ የሚሰጥዎት ቦታ ከመግባትዎ በፊት የት እንደሚኖሩ፡ የገንዘብ ድጋፍዎን እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ፡ እና በዚህ አዲስ ቤትዎ ችግር ካጋጠምዎት ማንን ማነጋገር እንደሚችሉ መረጃ ይሰጥዎታል። UKBA ወደ ማረፊያዎ ለሚያደርጉት ጉዞ ያመቻቻል ይከፍላል።

### ምን ዓይነት የመኖርያ ቤት ነው የማገኘው?

UKBA የሚሰጥዎ የመኖርያ ቤት የጋራ ቤት ወይም አፓርታማ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ቤቶችን የሚቆጣጠሩ ሰዎች ደግሞ ላንድሎርድስ (ባለቤቶች) ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ባለቤቶች ደግሞ የአልጋና ፡አስፈላጊዎቹ የማዕድ ቤት ዕቃዎች እንዲሰጥዎትና በአከባቢው የሚገኙት አገልግሎቶች እንዲያሳይዎት ሃላፊነት አላቸው። እንዲሁም የአከባቢው ዶክተር፣ ትምህርት ቤቶች ፣ እና/ወይም ኮሌጆች ያሳይዎታል ። በተጨማሪም እነዚህ ባለቤቶች፡ የሚኖሩበትን ቤት በደንብ የታደሰ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ስለ መኖርያ ቤቱም አካባቢው ከሚገኙ አገልግሎቶች የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ከባለቤቱ ወይም ከዋን ስቶፕ አገልግሎት (One Stop Service) ጋር መነጋገር አለብዎት። መገንዘብ የሚገባዎት ነገር ደግሞ ከማያውቁት ሰው ጋር አብረው በጋራ እንዲኖሩ ሊደረግ ይችላል።

### በዚህ የUKBA መኖርያ ቤት ለምን ያህል ጊዜ እቆያለሁ?

UKBA በዚህ የሰጥዎትን የመኖሪያ ቤት እንዲለቁ ትዕዛዝ ካልሰጥዎት በስተቀር፡ በመኖርያ ቤቱ እንዲቆዩ ይፈልጋል። ነገር ግን ከመኖርያ ቤቱ ያለ ፍቃድ በፍላጎትዎ ከለቀቁ፡ ከ UKBA ያገኙት የነበረውን የገንዘብና የመኖርያ ቤት እገዛ በሙሉ ይቋረጣል። ስለሆነ ከዚህ በ UKBA የተሰጥዎትን ቤት ለመልቀቅ ከፍለጉ፡ የUKBA ጽህፈት ቤትን አስቀድመው ማሳወቅ ይገባል። የUKBA ጽሕፈት ቤት የጥገኝነት ጥያቄዎ ውሳኔ እስኪሰጡ ድረስ በተሰጥዎትን የመኖሪያ ቤት ሊቆዩ ይችላሉ። የ UKBA ጽህፈት ቤት እንደ ስደተኛ ከተቀበልዎት፡ ይህ ያገኙት የነበረውን እገዛ ከ 28 ቀናት በኋላ ያቆማል። ይህ ማለት ደግሞ በ28 ቀናት ውስጥ መልቀቅ አለብዎት።

### የጥገኝነት ይግባኝ ካደረኩ ይህ ከ UKBA የማገኘው እገዛ ይቀጥላል?

አዎ። የ UKBA ጽህፈት ቤት ማመልከቻዎን ካልተቀበልዎትና ጽሕፈት ቤቱ በፈቀደው የጊዜ ገደብ መሰረት የይግባኝ ማመልከቻ ካስገቡ፡ በመኖርያ ቤቱ እንዲቆዩና ያገኙት የነበረውን ድጋፍም እንዲቀጥል ይደረጋል።

### የጥገኝነት ይግባኜ ተቀባይነት ካላገኘ UKBA ይደግፈኛል?

ከ18 ዓመት በታች ያሉ ጥገኛ ልጆች ካልዎት እና የይግባኝ ጥየቃዎ ተቀባይነት ባያገኝ እንኳ ያገኙት የነበሩት እገዛዎች መቀጠል ይገባዋል።

ከ18 ዓመት በታች ያሉ ጥገኛ ልጆች ከሌልዎት እና በዚህ የጥገኝነት ጥየቃ ሂደት ላይ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ከደረሱና ይግባኝ ለማለት መብት ከሌልዎት፤ UKBA ያገኙት የነበሩትን እገዛዎች ይህ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጥዎት ከ 21 ቀናት በኋላ ያቋርጠዋል።

ሆኖም ግን፡ የክፍል 4 ድጋፍ (Section 4 support) ማመልከት ይችላሉ። ስለዚህ ድጋፍ መረጃ ከፈለጉ ቀጥሎ ባለው ድረገፅ ላይ www.refugeecouncil.org.uk የጥገኝነት እገዛ ትብብር (Asylum Support Partnership) የሚለውን በራሪ ወረቀት አርዕስት ላይ 'በጥገኝነት ጉዳይዎ መጨረሻ ምንም ገቢ የሌልዎት ንዎትን?' የሚለውን በራሪ ጽሁፍ ለማንበብ ይችላሉ ወይም ስኮትላድ ላይ የሚኖሩ ከሆኑ ደግሞ Scottish Refugee Council leaflet 'ሴክሽን 4 ድጋፍ የሚለውን ጽሁፍ ለማንበብ ይችላሉ። ለዚህ ድጋፍ ማመልከቻ ለማድረግ የህግ አማካሪዎ ወይም በአቅራብያዎ የሚገኝ የስደተኞች ማህበር ሊተባበርዎት ይችላል።

## የሚያስፈልገኝ የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነው

በመኖርያ ቤት አገልግሎት የማይቸገሩ ከሆኑ፡ ለምሳሌ ከጓደኞችዎ እና ዘመድዎ ጋር የሚኖሩ ከሆኑ፡ የገንዘብ እገዛ ብቻ ለማግኘት ወደ UKBA ለማመልከት ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ የUKBA ጽሕፈት ቤት ያቀረቡትን ማመልከቻ በተመለከተ ውሳኔ ለመስጠት ጥቂት ሳምንታት ይወስድባቸዋል። በዚህ ጊዜ ምንም አይነት ድጋፍ ኣይሰጥም። ስለሆነም ተመላሽ ክፍያ ኣይኖርም ማለት ነው። መጨረሻ ላይ UKBA የገንዘብ እገዛውን ሊሰጥዎት ከተስማማ፡ የሚከተሉትን ነገሮች ይፈጸማሉ፤

1. የገንዘብ እገዛ ለማግኘት እንደተፈቀደልዎ የሚገልጽ ደብዳቤ UKBA ይልክልዎታል።
2. ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍ ኩፖኖች በመባል የሚያውቁትን የድንገተኛ ጊዜ አደጋ የድጋፍ ኩፖኖች ይሰጥዎታል። እነዚህ ኩፖኖች ደግሞ ለትንሽ ጊዜ ብቻ ያገለግላሉ። ወደ ፓስታ ቤት በመሄድ ደግሞ ወደ ገንዘብ ሊቀዩሩዋቸው ይችላሉ።
3. የማመልከቻ መመዝገቢያ ካርድ (Application Registration Card - ARC) ከተሰጥዎት ግን፡ ወደ ተመደበሎት ፓስታ ቤት በመሄድ ካርዱን አሳይተው የሚሰጥዎትን ገንዘብ ለመሰብሰብ ይችላሉ። ገንዘቡን የሚሰጥዎት ጽሕፈት ቤት የትኛው ፖስታ ቤት ሄደው ገንዘብዎን ለመቀበል እንደሚችሉ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይልክልዎታል።

ስለሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካልዎት ወይም የሚቸገሩ ከሆነ፡ ወደሚቀጥለው የUKBA የእገዛ መስመር ደውለው ለመጠየቅ ይችላሉ፡ **0845 602 1739** ወይም በአቅራብያው የሚገኘውን የዋንስቶፕ አገልግሎት (One Stop Service) መጎብኘት ይችላሉ። እባክዎን ይህ ለገንዘብና መኖርያ ቤት ድጋፍ ለሚያገኙ ሰዎችም የሚመለከት መሆኑን ያስተውሉ።

### ኩፖኑ ወይም የ ARC ካርድ ከጠፉብኝ ምን ይከሰታል?

ይህን ኩፖን ወይም ARC ካርድ ከጠፉብዎት፣ ከተሰረቀብዎት፡ ሌላ አዲስ ኩፖን ወይም የ ARC ካርድ ለማግኘት፡ የጠፋና የተሰረቀ ዕቃ የሚመለከትበት ፖሊስ ክፍል ሪፖርት ማድረግ ይገባዎታል። ከፖሊስ ጣብያው ደግሞ የወንጀል መለያ ቁጥር፡ የመዝጋቢው ፖሊስ ስም እና የፖሊስ ጣብያው ስም የያዘ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማምጣት አለብዎት። ይህ ደብዳቤ ደግሞ ወደ UKBA ጽህፈት ቤት ስኮትላንድ በ **020 8633 0653** ወይም 08703369233 የፋክስ ቁጥር ማድረግ ወይም ወደ አቅራብያው ወደሚገኝ የዋን ስቶፕ አገልግሎት ጽህፈት ቤት ማነጋገር ይገባል።

ገንዘብ የሚቀበሉበት ፖስታ ቤት ለመቀየር ከፈለጉ ወይም በ ARC ካርድዎን በመጠቀም ገንዘብዎን የማግኘት ችግር የሚያጋጥምዎት ከሆነ፡ የእገዛ መስመር በሆነው  ስልክ ቁጥር **01276 687 099** ደውለው ማነጋገር ይችላሉ። እንግሊዘኛ ቋንቋ የማይችሉ ከሆኑ፡ UKBA ስልክ ለመደወል አስተርጓሚ ወይም ጓደኛ እንዲተባበርዎት መጠየቅ አለብዎት።

### ያለሁበት ሁኔታ ተለውጧል
ሁኔታዎ ተቀይሮ በአሁኑ ጊዜ የመኖርያ ድጋፍ  እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ጭምር የሚያስፈልግዎት ከሆነ፡ ለዚህ ተጨማሪ የመኖርያ ድጋፍ በፈለጉበት ጊዜ ለማመልከት ይችላሉ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ፡ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የስደተኞች ማህበር በመሄድ ለማነጋገር ይችላሉ።

## UKBA ምን አይነት ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጠኝ ይችላል?

### የእናትነት ክፍያ
ልጅ ከወለዱ ለአዲስ ልጅዎ የሚሆን ከ UKBA ለተጨማሪ እርዳታ ለማመልከት ይችላሉ። ይህ እርዳታ ደግሞ ለአንድ ግዜ የሚሰጥ የ £300 ኩፖን ነው። ልጅ ለመውለድ በሚጠብቁበት ከአንድ ወር በፊት ወይም ልጁ ከተወለድ በኋላ ባሉት ሁለት ሳምቶች ውስጥ በጽሁፍ ማስገባት ይኖርብዎታል። ማመልከቻውን ለመውለድ በሚጠብቁበት ግዜ በፊት የሚያስገቡት ከሆነ ማረጋገጫ ማቅረብ ወይም ልጁ ከተወለደ በኋላ ከሆነ ደግሞ የልጁን የልደት ማስረጃ ማቅረብ ይገባል። እንግሊዝ ኧገር ከመወለዳቸው በፊት ከሶስት ወር ወይም ከዛ ያነሰ ጊዜ የሚወለዱ ህፃናቶች ለዚህ የወሊድ እርዳታ ለማግኘት ብቁ ናቸው። ማስታወስ ያለብዎት ነገር ግን፡ የሴክሽን 4 ድጋፍ የሚያገኙ ሰዎች ግን እስከ £250 ፓውንድ በቶከን መልክ ይቀበላሉ።

### ለእጉዝ እናቶችና ህፃናቶች የሚሰጥ ክፍያ
የ UKBA  እገዛ የሚቀበሉ እርጉዝ እናቶች ወይም ከአንድ እስከ ሶስት ዓመት የሆኑ ህፃናቶች ያሏቸው ቤተሰቦች፡ ከ UKBA የሚያገኙት መሰረታዊ እገዛ በላይ የ £3 ተጨማሪ ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው። ከአንድ ዓመት በታች የሆነ ህፃን ያላቸው ደግሞ በሳምንት £5 ተጨማሪ ይሰጣቸዋል። እነዚህ ክፍያዎች የክፍል 4 ድጋፍ የሚያገኙትም ይመለከታቸዋል።

### ለጥገኝነት ወይም ለይግባኝ  ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሚደረጉ ጉዞዎች
እገዛ የሚቀበሉ ከሆኑ፡ UKBA ለጥገኝነት ወይም ለይግባኝ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ በሚጓዙበት ጊዜ፡ የጉዞዉን ወጪ ይከፍልልዎታል። ለዚህ የጉዞ ወጪ ለመክፈል እገዛ እንዲሰጥዎት ማመልከት ይችላሉ። ይህንን ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ የዋን ስቶፕ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ሊተባበርዎት ይችላል።

## ሌሎች መረጃዎች

### የ UKBA ጽሕፈት ቤት ሊረዳኝ የማይፈልግ ከሆነስ? ወይም ድጋፌን ለማቋረጥ ካስፈራራኝስ?
UKBA እርስዎን ለመርዳት እምቢ ካለ፡ ጉዳይዎን ወደ ዳኛ አቅርበው ይግባኝ የማለት መብት አለዎት። ነገር ግን ጉዳይዎ እስኪጣራ ድረስ ከ UKBA የሚያገኙት ምንም እገዛ አይኖርም። ‘በተቻለ መጠን በፍጥነት’ ይግባኝ ባለማለታቸው ምክንያት ጥገኝነታቸው የድጋፍ ተቀባይነት ያላገኙ የጥገኝነት ፈላጊዎች ምንም የይግባኝ መብት የላቸውም።

ሆኖም ግን፣ ድጋፍ እየተቀበሉ ከሆነና UKBA ይህ ድጋፍ እንደሚቋረጥ ካስታወቅዎት፣ ይግባኝ የማለት መብት ሊኖርዎት ይችላልእና ድጋፍዎ በይግባኝ ሂደቱ ላይ ይቀጥላል።  በጥገኝነት ድጋፍ ይግባኝ ላይ ለበለጠ መረጃ ፣ እባክዎ የጥገኝነት (Asylum Support Appeals Project) ድጋፍ ይግባኝ ፕሮጀክት ፋክትሺቶችን በ፡ www.asaproject.org.uk ላይ ይመልከቱ ።

### ለመንቀሳቀስ እችላለሁኝ?
እንግሊዝ አገር (UK) ውስጥ ወደ ፈለጉበት ቦታ ለመንቀሳቀስ ይችላሉ፡ ነገር ግን በ የUKBA መኖርያ ቤት የሚሆሩ ከሆኑ፡ አከታትለው ከሰባት ቀንና ለሊት ወይም በስድስት ወር ጊዜ ከ 14 ቀናት በላይ ቤቱን ለቀው ለመሄድ አይፈቀድም። የመኖርያ ቤቱን  ለቀው ለጊዜው የሚሄዱ ከሆነ፡ ባለቤቱን ማሳወቅ አለብዎት። UKBA።

### ለጥገኝነት ያቀረቡት ጥያቄ ውሳኔ እስኪሰጠኝ ድረስ ስራ ለመስራት እችላለሁኝ?
በተለምዶ ጥገኝነት ጠያቂዎች ስራ ለመስራት አይፈቀድላቸውም። ነገር ግን፡ የጥያቄዎ የመጀመርያ ውሳኔ እስኪሰጥዎት ድረስ ከአንድ ዓመት በላይ የጠበቁ ከሆነ፡ ስራ ለመሰራት ፍቃድ እንዲሰጥዎት ለማመልከት ይችላሉ። የህግ ኣማካሪዎ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊተባበርዎት ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፡ በጥገኝነት ሂደት ውስጥ እያሉ አዲስ የሆነ ችሎታ ለማዳበር የሚረዳውን ነጻ የበጎ ስራ ለመስራት ይችላል። ይህ ዓይነት ስራ ደግሞ በፍቃደኝነት የሚሰራና የማይከፈልበት ስራ ነው። ሆኖም ግን፡ የነጻና የበጎ ስራ በሚሰሩበት ጊዜ ለጉዞና ለምሳ የሚያወጡት ወጪዎች አብዛኛው ጊዜ ይከፈልዎታል።

**አስፈላጊ ማስታወሻ**
የነበሩበት ሁኔታ ከተለወጠ፡ ለምሳሌ፡ የቤተሰብዎ አባል ከእርስዎ ከተቀላቀለ፣ አድራሻ ከቀየሩ፣ ወይም የነፍሰጡር እናቶች እገዛ ለማመልከት ከፈለጉ፡ በተቻለ መጠን ይህንን ከመሆኑ አስቀድመው የ UKBA ጽህፈት ቤት ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ሁኔታዎ እንዴት እንደተቀየረ በሚቀጥለው አድራሻ በመጠቀም ወደ UKBA ደብዳቤ ይጻፉ፡ እባክዎትን የዚህን ደብዳቤ ቅጂ ይያዙ። በአካባቢዎ የሚገኝ ከዚህ በታች የተጻፈው የስደተኛ ማህበር በዚህ ጉዳይ ላይ ሊተባበርዎት ይችላሉ።

## UKBA የእገዛና የምክር ምንጮች

ለጥገኝነት ጠያቂዎች የሚሆን ምክርና እገዛ የሚያቀርቡ ዋናዎቹ የስደተኞች ማህበሮች ጥቂቶቹ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፤ መልቲ ካልቸራል ሪሶርስ ሴንተር (Multi-Cultural Resource Centre)፡ ኖርዝ ኦፍ ኢንግላንድ ሪፊውጂ ሰርቪስ (North of England Refugee Service)፡ ሪፍዩጂ አክሽን (Refugee Action)፡ ሪፊዩጂ ካውንስል (Refugee Council)፡ ስኮቲሽ ሪፉዩጂ ካውንስል (Scottish Refugee Council)፡ እና ዌልሽ ሪፊዩጁ ካውንስል (Welsh Refugee Council) የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ማህበሮች ጥገኝነት ጠያዊዎችና ስደተኞች በትክክለኛ መንገድና በክብር መያዝ ይገባቸዋል የሚል ዓላማ አላቸው።

እነዚህ ማህበሮች እንግሊዝ አገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የዋን ስቶፕ አገልግሎት (One Stop Services) ጽህፈት ቤታቸው በኩል ስለ መኖርያ ቤት፣ ስላሉት የገንዘብ ድጋፎች፣ የጥገኝነት ጉዳዮችን፣ በጤናና ሌሎች ጉዳዮች ምክርና መረጃዎች ያቀርባሉ። እነዚህ ማህበሮች ከመንግስት ነጻ የሆኑ ማህበሮች ናቸው። ስለሆነም የነዚህ ማህበሮች አባል ሰራተኞች፡ ለራስዎ የሚጠቅምዎትን የምክር አገልግሎት ያቀርብልዎታል። ነገር ግን ጉዳይዎን አስመልክቶ በመንግስት የተሰጠ ውሳኔ ሊቀይሩ አይችሉም። እንደ የዜጎች የምክር አገልግሎት ፡ የአካባቢ የምክር ጽህፈት ቤት ወይም የስደተኛ ጓዶች ያሉ ሌሎች ማህበሮች ነጻ ምክሮችና መረጃዎች ይሰጣሉ።

**Multi-Cultural Resource Centre (Northern Ireland)**
Tel: 02890 238 645
www.mcrc-ni.org

**North of England Refugee Service Head Office (North East)**
Tel: 0191 245 7311
www.refugee.org.uk

**Refugee Action Head Office (East Midland, North West, South Central, South West)**
Tel: 020 7654 7700
www.refugee-action.org.uk

**Refugee Council Head Office (London, East of England, Yorkshire & Humberside, West Midlands)**
Free advice line: 0808 808 2255
Tel: 020 7346 6700
www.refugeecouncil.org.uk

**Scottish Refugee Council**
Tel: 0141 248 9799
Freephone: 0800 085 6087
www.scottishrefugeecouncil.org.uk

**Welsh Refugee Council**
Tel: 02920 489 800
www.welshrefugeecouncil.org

Asylum Support Partnership consists of:

North of England Refugee Service, charity number: 1091200 www.refugee.org.uk
Refugee Action, charity number: 283660 www.refugee-action.org.uk
Refugee Council, charity number: 1014576 www.refugeecouncil.org.uk
Scottish Refugee Council, charity number: SC008639 www.scottishrefugeecouncil.org.uk
Welsh Refugee Council, charity number: 1102449 www.welshrefugeecouncil.org